# 28 ቢሊዮን 469 ሚሊዮን ዶላሩ የት ገባ?

# 384 ቢሊዮን ብሩ ማለቴ ነው !

*ሲሣይ አጌና (አዲስ አበባ)*

*እ.ኤ.አ በ2008 ብቻ የኢህአዴግ መንግስት ከለጋሾች ያገኘው ድጋፍ 3ቢሊዮን 327 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፣ ይህን በአዲሱ ምንዛሪ ትተን በወቅቱ ምንዛሪ ወደ ብር ብንለውጠው 45 ቢሊዮን ብር ይመጣል፤በአጭሩ ይህ ገንዘብ ደርግ 17 ዓመታት ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በአጠቃላይ በእርዳታም፣በብድርም ፣በግብርም በሁሉም ከሰበሰበው ይበልጣል*

*ቀጣዩ ቀልድ ከዚህ ፅሑፍ ይልቅ «**በውሸት ደዌ ለምትሰቃዩ –እነሆ ዕውነቱን!...**» በሚል ርዕስ ቀደም ሲል ነሀሴ ላይ ለለቀኩት ፅሑፍ ይበልጥ የሚስማማ ይመስለኛል፤ሆኖም ቀልዱን እንድም በወቅቱ ላስታውሰው ባለመቻሌ፣በሌላም በኩል ይህ ፅሑፍ ምንም እንኳን በዋናነት በዓለም አቀፍ ዕርዳታዎች ላይ ቢያተኩርም እንደ ቀጣይ ክፍል ሊወሰድ የሚገባው በመሆኑ፣በሶስተኛ ደረጃ ግኑኝነት ባይኖረው እንኳን ቀልዱን ያልሰማችሁ ብትሰሙት ማለትም ብታነቡት ምን ጉዳት አለው? በሚል ከሱ ልጀምር፤*

ዓመት ያለፈው ይመስለኛል፤ አንዲት በእንግሊዝኛ የተፃፈች አጭር የፅሑፍ መልዕክት (SMS) ከአንዱ ሞባይል ወደ ሌላው እየተላከች ስትነበብ የነበረ ሲሆን፣ ውሸትን መሠረት ያደረገች ነበረች፤... ቃል በቃል የተላለፈውን መልዕክት ባላስታውሰውም ይዘቱን ግን በፍፁም የሚረሳ አይደለምና አልዘነጋሁትም፤አንድ ኢትዮጵያዊ በሞት ከዚህች ዓለም ይለይና እንደ ፅድቁ ብዛት ገሃነምን ሣይሆን መንግሥተ ሰማያትን ጎብኝቶ በጌታ ፍቃድ ወደ ምድር ይመለሳል፤ ይህ ከሞት የተነሳው ሰው በመንግሥተ ሠማያት ስለገጠመው ሁኔታ ለወዳጆቹ ሲያስረዳ እንደተናገረው ከሁሉ በላይ የገረመው የሰማይ ቤቱ ሰዓት ነው፤ምድር ላይ ባለው በእያንዳንዱ ሰው ስም ሰማይ ቤት የተቀመጠው ሰዓት ቅርጹ የሠዓት ይሁን እንጂ ጊዜ መቁጠሪያ ግን አይደለም::

የዚህ ሠዓት አገልግሎት ሰዎች በምድር ላይ ኃጢያት ሲሠሩ የሚመዘግብ ሲሆን፣ አንዴ በዋሹ ቁጥር የሰዓት ቆጣሪው ጢቅ እያለ አንድ ስቴፕ ይሄዳል፤ ሌላ ጊዜ ሲዋሽ ደግሞ አሁንም ሠዓቱ እንደገና ጢቅ እያለ ይቀጥላል፤...ታዲያ ምድር ላይ ካሉ ሠዎች እስከአሁን የሠዓቱ መቁጠሪያ ምንም ሣይንቀሳቀስ ባለበት የሚገኘውና ውሸት ያልተመዘገበበት የኔልሰን ማንዴላ እንዲሁም ጥቂት የማይታወቁ አትዮጵያዊያን እና ጥቂት የማይታወቁ የውጭ ዜጎች ብቻ ነው፤ሌሎች ጥቂት ንፁህ ሰዎች ከሃገራችንም ከውጭም ብዙ ስላልዋሹ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሰአቱ መዝግቧቸዋል፤...

በዚህ የሠማይ ቤት ሠዓት መሠል የሐጢያት መቁጠሪያ፣የውሸት መመዝገቢያ ማብራሪያ የተ ደመመና በኢሕአዴግ ሰዎች ውሸት የተንገፈገፈ አንድ ግለሠብ ***«ኧረ ለመሆኑ የኢህአዴግ ሰዎች ሠዓትስ እንዴት ነው? ምን ያህል ጊዜ ጢቅ ብሏል?»*** ብሎ ሲጠይቅ ከሠማይ ቤት የተመለሰው ግለሰብ ***«የእነርሱ ውሸት ያለማቋረጥ ስለሆነ ሰዓቱም ያለማቋረጥ ይዞራል፣ ጌታ ክፍል ውስጥ እንደ ቬንትሌተር የሚያገለግለው የእነርሱ ሠዓት ነው»*** ሲል መለሰ፡፡ ይህንን ከሞባይል አጭር የፅሑፍ መልዕክት (SMS)

ላይ ካነበብን ሠነበትን፣ ምን መሠንበት ብቻ ከረምን፤ግን ውሸቱ እየበረታበት እንጂ እየቀነሠ ባለመሆኑ... ዛሬ ደግሞ ቬንትሌተሩ ከፍጥነቱ ብዛት ከአገልግሎት ውጭ ሣይሆን ይቀር ይሆን?...

የኢህአዴግ ሠዎች ያልተቋረጠ ውሸት በዋናነት የሚስተጋባው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነው፤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ደግሞ ወ/ሮ ሶሎሜ ታደሰ የጣቢያውን ኃላፊነት ከለቀቁበት ከ1994 ወዲህ ከውሸቱ ጎን ለጎን ይካሄድ የነበሩ አዝናኝ ፕሮግራሞች ርቀውታል፤ውሸቱ ብቻ ተጠናክሮ መዝናኛው በአፍጢሙ ተ ደፍቶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት «ሚኒ ሚዲያ» በመምሰሉ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን **«እንደምን አመሻችሁ ዲሽ የሌላችሁ»** እየተባለ የሚቀለድበት ከሆነ ዓመታት ተቆጠሩ፤ ዕውነቱን ለመናገር ዲሽ የሌላቸውም ዜጎች በርካሹ የቻይና ዲቪድ ማጫወቻ በአንድ ብር የኪራይ ፊልም ከስቃይ ተርፈናል በማለት ከኢትዮጵያ ቴሌ ቪዥን ማምለጫ ማግኘታቸውን በእፎይታ የሚያነሱበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፤ **«ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር በአራት አመት አንዴ ከዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ ጋር ነው የምንገናኘው** » የሚሉ ሰዎችን ማግኘት እንግዳ ነገር አይደለም፤ ይሁንና ዕድሜ ለ «ገመና» ድራማ እሁድ-እሁድ ከሰዓት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በብዙዎች ቤት የመታየት ዕድል ገጥሞታል፡፡ ...

ዓመታት በዘለቀወና የዕለት ተዕለት ተግባር ሆኖ በቀጠለው የኢህአዴግ የከሸፈ የፕሮፓጋንዳ ስልት ብዙ በመዋሸት ጭላንጭሉንም ዕውነት እየጋረደ እንጂ ብርሃን ሲፈነጥቅበት አይታይም፤በዚህም የተነሳ ለሚታዩ አንዳንድ የመንገድ ግንባታ ጀምሮች እንኳን ሕዝባዊ እውቅናን ሊጎናፀፍ አልቻለም፡፡በምርጫ 2002 ክርክር ወቅት አንዳንድ ተቃዋሚዎች ***«ምን መንገድ መንገድ ትላላችሁ፤ ጣሊያኑም እኮ ከእናንተ የበለጠ መንገድ ሠርቷል? ደግሞ የት የሠራችሁት መንገድ ነው ? »*** እስከ ማለት የሔዱበትን የሚጋራ ሕዝባዊ አስተያየት መኖሩን ቢያንስ አዲስ አበባ ውስጥ ላለነው ግልጽ ነው፤*«መንገድን እንበላዋለን ወይ?»* የሚለው ይበልጥ የሚሠማው አስተያየት ሲሆን፣ እንደ ቀልድ ተደርጎ የሚነሣው ደግሞ ***«በ97 ምርጫ ወጣቱ ያስቸገራቸው ድንጋይ እየወረወረ በመሆኑ አሁን አስፋልት እያደረጉት ያሉት ድንጋዩን ለማጥፋት ነው»*** እስከ ማለት የዘለቁ ፌዞች ተሰምተዋል፤... እርግጥ ነው ***«የመንገድ መንግስት»*** በማለት በቅሬታና በጥላቻ ውስጥም ሆነው ዕውቅና የሚሠጡ ደጋፊዎቹ ብቻ ሳይሆን ጥቂትም ቢሆኑ ተቃዋሚዎችም መኖራቸው እርግጥ ነው፡፡... እርግጥ ነው የኢህአዴግ መንግስት ከምርጫ 97 በኋላ በተለይ በአዲስ አበባ የከተማዋን ደረጃ ከፍ የሚያደርጉና የትራፊክ ፍሰቱን የሚቀላጥፉ ሠፋፊ መንገዶችን ሠርቷል፤ እየሰራም ነው፤(በተለይ በክረምቱ ነባር መንገዶች እየፈራረሱ ትልልቅ ጉድጓዶች እየበረከቱ ችላ መባላቸው ባይገባንም) በርከት ያሉ ሕንፃዎች እየተገነቡና በመገንባት ላይም ይገኛሉ፤በከተማው ያለውን የቤቶች ችግር ለመፍታት የኮንዶሚኒየም ቤቶች በብዛት እየተሰሩ መሆናቸውም እርግጥ ነው፡፡...

ነገር ግን ኢህአዴግና ደጋፊዎቹ አብዝተው እንደሚያወሩለት እነዚህ ግንባታዎች እንደ ተዓምር የሚቆጠሩና ከሌሎች የአፍሪካ ሐገሮች ፊት የሚያስቀድሙን ናቸውን? እነዚህ ክንውኖች የኢህአዴግ መንግስት ባይሆን ኖሮ የማይሠሩ ናቸው? ኢሕአዴግ ከቀደሙት የኢትዮጵያ መንግስታት በተለየ ለዚህች ሐገር ልማትና ብልፅግና የተጋና እየተጋ የሚገኝ መንግስት የሚያሠኘው ነውን ? ከሁሉ በላይ ቀድሞ መነሳት

የሚገባው ነጥበ የመብትና የነጻነት ጥያቄ የዳቦና የመጠለያ ጥያቄ ብቻ አለመሆኑ ሲሆን፣ሌላው መነሳት የሚገባው ጉዳይ አቶ መለስ ዜናዊ የሚመሩት የኢሕአዴግ ቡድን ከምርጫ 97 ወዲህ ወደ ስልጣን የመጣ ቡድን አለመሆኑ ነው፤ይህ ቡድን የምርጫ 97 ን የዲሞክራሲን ፈተና በጉልበት ተሻግሮ፣ከ97 በፊት የነበረውን ከፊል ነፃነት ሽሮ በጉልበት እየገዛ ያለ መንግሥት መሆኑም መታወቅ ይኖርበታል፤የኢሕአዴግ መንግስት በዚህች ሐገር የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የወጣውና ሐገሪቱን ማስተዳደር የጀመረው ከ19 ዓመታት በፊት ጀምሮ ሲሆን፣ ብዙ እየተነገረለት የሚገኘው በምርጫ 97 ዋዜማና ማግስት እየተከወኑ የሚገኙ አንዳንድ ግንባታዎችን የተመለከተ ነው፤ ኢሕአዴግ ከ1997 በፊት በሐገሪቱ ላይ የልማት እንቅስቃሴዎችን ያላደረገው ለምንድነው? ከ1997 ወዲህስ ይህኛውን መንገድ የመረጠበትስ ምክንያት ምንድነው?እየተሰራ ያለው በማን አቅም ነው? መሰራት የሚገባውን ያህል ተሰርቷል? የሚለውን መመርመሩም የሚባለውን ልማት ቀጣይነትም የሚመልስ ይሆናል፡፡

ከ1997 በፊት ለሐገሪቱና ለሕዝቧ (እነርሱ ከሌላ የበቀሉ ይመስል) ባለባቸው ጥላቻ ወይንም በሌላ ምክንያት ስላልሠሩ ከ1997 በኋላ ለሚሠሩት ተግባር እውቅና መንፈግ ተገቢ እንዳልሆነ አምናለሁ፣ በ2002 የምርጫ ክርክር ወቅት ግንባታዎችን በተመለከተ በአንዳንድ ፓርቲዎች ሲነሳ የነበረውና በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በስፋት የሚሠማው «**ዕድሜ ለቅንጅት**» የሚል ነው፤ኢሕአዴግ ሕዝቡ በምርጫ ድምፅ ስለነፈገውና በተለይ በአዲስ አበባ አንዲት ወንበር እንኳን ሣይተርፈው በዜሮ ስለሸኘው የሕዝብ ልብ ለማሸነፍ ሲል የጀመረው ስለመሆኑ መገመት የሚቻል ሲሆን፣ መሪዎቹ የሚሰጡት መግለጫም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነበር፤«***ሕዝቡ በምርጫው ቢጫ ካርድ ስለሰጠን ጥፋታችንን እየረምን ነው***» ሲሉ በተደጋጋሚ ተደምጠዋል፡፡

አንድ ሐገራዊ ኃላፊነትን የያዘ አካል ወይንም ቡድን እንኳንስ ከዛ ሕዝብ ውስጥ የበቀለ ይቅርና ለቅኝ ግዛት የመጣ ወራሪም የራሱን ጥቅም ለማሳካት ሲል የሕዝብን ስሜት ለማሸነፍ በጎ ተግባራትን ማለትም የልማት ሥራዎችን መከወን ለሕልውናውም እጅግ ወሳኝ ነው፤ይህ ማለት ደግሞ ሕዝባዊ ተቀባይነትን ያስገኛል ማለት እንዳልሆነም በደማቁ ሊሰመርበት ይገባል፤ኢሕአዴግ አይችልም እንጂ አዲስ አበባን ኒውዮርክ ቢያደርጋት እንኳን የሕዝቡን መብትና ነጻነት እንዲሁም እኩልነት እስካልመለሰ ድረስ በነጻ ምርጫ ሊያሸንፍ አይችልም፤ተቃዋሚዎች በወጉ ባልተደራጁበትና ባልተሰባሰቡበት የ2002 ምርጫ እንኳን ሂደቱ በአፈናና በተፅእኖ መሞላቱ የኢሕአዴግ መሪዎችና ሕዝቡ መነቃቃታቸውን ያሳያል፡፡

የተነሳሁበትን ነጥብ ግልፅ ለማድረግ ኢህአዴግ ባለፉት 5 ዓመታት በተለይም ከምርጫ 97 ወዲህ፣ ጥቂት የሚታዩ የልማት ጅምሮችን የከወነ ሲሆን፣ አስገራሚው ነገር በቀደሙት ዓመታት ኢህአዴግ ራሱ አለማልማቱ ብቻ ሳይሆን የግል ባለሐብቶች ለሐገሪቱ ልማት ተገቢ አስተዋፅኦ እንዳያደርጉ ሁሉን ነገር በመቆጣለፉ የግል ባለሐብቶች እንኳን ብድር፣ መሬት በማግኘት ወዘተ በተሻለ መንቀሳቀስ የሚችሉበት ዕድል የተፈጠረው ከምርጫ 97 በኋላ ነው፣ ኢሕአዴግ ከምርጫ 97 ጀምሮ የልማት ሥራዎችን እያሳየ መሆኑ ላይ ጥያቄ ማንሣት ዕውነትን መካድ ሲሆን፣ ሊሠራ ከሚገባው አንፃር ካየነው ደግሞ ምንም እየተሠራ

እንዳልሆነ በተጨባጭ መመልከት ይቻላል፡፡

ሕሊናቸውን በሆዳቸው የከለሉ የከተማ ኢሕአዴጎች እንደሚሉት የኢህአዴግ መንግሥት ከቀደሙት የኢትዮጵያ መንግስታት በበለጠ ለዚህች ሐገር ሠርቷልን? ይፋዊ መረጃዎች በጭራሽ የሚል መልስ ይዘዋል፤ የቀደሙት የኢትዮጵያ መንግስታት ይህ ነው የሚባል የውጭ እርዳታ ባላገኙበት፣ የሐገሪቱ ዓመታዊ በጀት ከ60 ፐርሰንት በላይ ለጦርነት እየዋለ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ በራስ አቅም የሠሯቸውን የልማት ርምጃዎች በዚህ መንግሥት በራስ አቅም እንዳልተሠሩ በተጨባጭ ማሣየት የሚቻል ሲሆን፣ ለምን የሚለውን መጠየቅና መመርመር የራሱ የኢህአዴግ ሠዎች ሥራ ነው፤ ኢሕአዴግ ሥል የአቶ ስዬን አባባል ልዋስና ከድል በኋላ በእህል ውሃ ተሸንፈው፣በዓላማ ሣይሆን በጥቅም አባል የሆኑትን አይጨምርም፤በተከለለ ሕሊና ዕውነት አትፈካም እና እነሱ እንዲቸገሩ አልፈልግም፡፡

...ስለ ኢህአዴግ ተዓምራዊ እድገት የሚጠቀሱት በአዲስ አበባ የተሰሩ መንገዶች (በተለይም የጎተራው ዘመናዊ መሽጋገሪያ-inter-change)እንዲሁም የቅርቦቹ የግልገል ግቤ 2፣የተከዜና የጣና በለስ የሃይል ማመንጫዎች፣በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡና በመገንባት ላይ ያሉ ሕንጻዎች ፣የዓባይ ድልድይ (ሕዳሴ ተብሏል)አይደሉምን ? አይኑን ገልጦ ለመረመረ ኢሕአዴግ በከወናቸውና ባስከወናቸው በእነዚህ ግንባታዎች የሚፈጠርበት ኩራት ሣይሆን አጥንት ድረስ የሚዘልቅ ንዝረትና ዕርዳታው ሁሉ የት ገባ የሚል ቁጭት ነው፤በእርዳታና በብድር ከተገኘው ወደ 400 ቢሊዮን ብር እስካሁን ለተጠቀሱትና ለሌሎች የወጣው 80 ቢሊዮን ብር እንኳን አልሞላም፤ከ300 ቢሊዮን ብር በላይ የት ገባ ?

«አዲስን በ24 ሠዓት» በሚል በቅርቡ ማለትም ከነሐሴ/2002 አጋማሽ ጀምሮ ተደጋግሞ በቀረበ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ከአሜሪካን ሐገር ከ21 ዓመት በኋላ ተመለስኩ የሚሉ ግለሠብ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ካሜራ ማኖችና ጋዜጠኞች ታጅበው አዲስ አበባን እስከ ሌሊት 6 ሠዓት አብረው በማሣለፍ የሰሩትን ፕሮግራምም ተከታትለናል፤እኚህም ሰው ያው እንደ ኢሕአዴጎች ስለ መንገድ ግንባታው ተአምራዊነት፣ ስለህንፃዎቹ ብዛት፣ቁመት እና ማማር ነግረውናል፤በማሌዢያ ኳላላምፑር የሚገኘው ፔትሮናስ (መንታ ሕንጻዎች) እና የዱባዩ ቡርጅ ከሊፋ ታወር በአዲስ አበባ የተገነቡ እስኪመስለን፡፡ታዋቂው አትሌት ኃይሌ ገ/ስላሴም የአዲስ አበባ መንገድን ከናይሮቢ ጋር በማነፃፀር የተሻለ ስለመሆኑ ሲናገር አድምጠነዋል፤ ማነፃፀሪያው ናይሮቢ ኤርፖርት ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ ረዥም ሲሆን፣ የአዲስ አበባ አጭር መሆኑን ነው፡፡

የናይሮቢ ኤርፖርት ከከተማዋ እንብርት ያለውን ርቀት፣ እንዲሁም በናይሮቢ ጎዳና የሚርመሰመሱ መኪናዎችን ብዛት በአጠቃላይ በመላ ሐገሪቱ 3መቶ 20 ሺህ ብቻ መኪና *(የሚያዚያ 2002 የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን መረጃ)* ካለባት ኢትዮጵያ ጋር በማነፃፀር ምኞትን ሳይሆን እውነትን መናገር ይበልጥ ትልቅ ያደርጋል፤ 40 ሚሊዮን ሕዝብ ያለባት ኬኒያ ከአንድ ሚሊዮን በላይ መኪና ሲኖራት፣ከዚህ ውስጥ ከ600 ሺህ የሚበልጡት የሚርመሰመሱት በናይሮቢ ጎዳናዎች ላይ ነው፤ከ 80 ሚሊዮን የሚልቅ ሕዝብ ያላት ኢትዮጵያ በጠቅላላ ካለት መኪና ዕጥፍ የሚሆኑት በናይሮቢ ጎዳናዎች እንደሚገኙም መዘንጋት

የለበትም፤ኬኒያ በዓመት ከ አንድ ሚሊዮን በሚበልጡ ቱሪስቶች የምትጎበኝ ሀገር በመሆኗም ወደ አውሮፕላን ማረፊያው የሚወስዱ መንገዶች መጨናነቅ የዚህም ውጤት ነው፤(በ2008 1ሚሊዮን 65 ሺ 8 ቱሪስት ኬኒያን ጎብኝቷል) ኬኒያ በፈረንጆች 2008 ብቻ አዲስ ሰሌዳ የሰጠቻቸው መኪናዎች ብቻ ከመቶ ሺህ በላይ ሲሆኑ፣በትክክል ለማስቀመጥ 121 ሺ.831 ነው፤ይህም በኢትዮጵያ ካሉት ጠቅላላ መኪኖች ከአንድ ሶስተኛ በላይ ነው፤ኃይሌ ይህንን ግንዛቤ ውሥጥ ማስገባት ነበረበት፤መንገድንም በተመለከተ ኬኒያ ከሀገሪቱ ቆዳ ስፋት 1.57 በመቶውን ያህል ስትሸፍን ኢትዮጵያ ከኬኒያ ሶስት ዕጥፍ በታች 0.50 ላይ መሆኗንም ማወቁ አይከፋም፡፡

ርግጥ ነው ኃይሌ ትልቅ ሠው ነው፤ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ደግሞ ታላቅነቱ የእጅግ ወሳኝ ወቅት ክስተት ነው፤የኢትዮጵያ ባንዲራ ኢትዮጵያን ለመምራት መጣን የሚሉ ሠዎች ባረከሠቡት እና በጨርቅነት በተመነዘረበት ወቅት የብዙዎችን ሃዘን የመለሠ፣እንባቸውን ያበሰ ታላቅ ባለውለታችን ነው፤ኃይሌ የተግባር እና የስኬት ሰው ነው፤ኃይሌ ገ/ስላሴ የአገር ሽማግሌ ሆኖ ከነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ጋር እያደረገ ባለው ብዙዎችን ባሳዘነው እና ብርቱካን ወህኒ ቤት ተቆልፎበት እንድትቀር ባሳዩት ግዴለሽነት እና እውነትን ለመጋፈጥ ባሳየው ሽሽት ማንም ምንም ሲለው ያልታየው ብሔራዊ ጀግናችን፣ ያውም በወሳኝ ቀን የተገኘ ባለውለታችን በመሆኑ ነው፤በኢሕአዴግ ጉባኤ መገኘቱ እና ለኢሕአዴግ ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ ሪከርድ የሰበረበትን ማሊያ መሸለሙ መብቱ ቢሆንም፣ብርቱካን ተቆልፎባት እንድትቀር ያሳየው ግዴለሽነት ከግዴለሽነትም በላይ የአቋም ጉዳይ ነው ወይ የሚል ጥያቄም ያስነሳ ይሆናል፤

እንደ ኃይሌ የተለያዩ ዓለማትን የዞሩ፣ በተለይም የቅርቦቹን የአፍሪካ ከተሞችን እነ ካይሮን፣ ናይሮቢን፣ ካርቱምን የጎበኙ ወይዘሮ አዲስ አበባን ከሌሎች ከተሞች ማወዳደር እጅግ ከባድ መሆኑን በዚያው ሀይሌ በቀረበበት ፕሮግራም ላይ ገልፀዋል፤ ለሐገራቸውና ለከተማቸው ያላቸውን ፍቅር ግን ***«አዲስ አበባን ስለምወዳት ለእኔ ከሁሉም ትበልጥብኛለች»*** በሚል አስቀምጠዋል፤እውነትን መናገር ያስከብራል፤ የራስ የሆነ የራስ ነውና በርግጥም አዲስ አበባ አማረችም ጎሰቆለችም እንወዳታለን፤ከጉስቁልናዋ ለማውጣት ግን ልንረባረብላት ይገባል፤በስማችንም የመጣው ዕርዳታ እንዲሁም ያልተወለዱ ልጆቻችን ጭምር የሚጠየቁበት ብድር በአግባቡ ሥራ ላይ ሊውል ግድ ይላል፡፡

ስለ ኢህአዴግ የግንባታ እንቅስቃሴ ሲወሳ ማተኮር ያለብን የመንገድ እና መሰል ግንባታወዎችን እንጂ ህንፃዎችን እንዳልሆነም ማስታወሱ ተገቢ ነው፤ህንፃዎች በአብዛኛው «በግል ባለሐብቶች» የሚሠሩ ሲሆን፣ እነሱም እንደመንገዱ ሁሉ ከምርጫ 97 በኋላ መንግስት የባንክ ብድር ለቀቅ በማድረጉ እና አንፃራዊ ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩ ያቆጠቆጡ ናቸው፤ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን ዕድል ቢያመቻች ኖሮ ዛሬ የት በደረስን ነበር፤ከ14 ዓመታት በኋላ ኢሕአዴግ እንዴት ከእንቅልፉ ነቃ ? እንዴትስ ወደዚህ መስመር ገባ ? ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ሕዝባዊ ድጋፍ እንደሌለው በተጨባጭ ካረጋገጠና የጉልበቱን መንገድ አጠናክሮ ከያዘ በኋላ ***«ዲሞክራሲ የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን የሕልውና ጉዳይ ነው»*** የሚለውን ከ1994 ወዲህ ያነገበውን መፈክር በግልፅ ሲጥለው፣በሥልጣን ለመቆየት አማራጭ አድርጎ የወሠደው የልማት ሥራዎችን

በማጠናከር *«ልማታዊ መንግስት»* የሚል ስያሜ መያዝን ነው፤በዚህ ጉዞ ላይ የምዕራባዊያን ጫጫታ እንደሚመጣ፣እርዳታ ማቆምም እንደሚከተል ሆኖም የፈለገው ቢሆን አማራጩ ይህ ብቻ ነው ብሎ ከ 4 ዓመት በፊት ወስኖ መንቀሳቀሱን ከግንባሩ የትንታኔ መፅሔት እንረዳለን፡፡

ኢሕአዴግ የምርጫ 97ትን ሕዝባዊ፣ሠላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በጉልበት ከደፈጠጠ በኋላ በሐገር ውስጥና በውጭ የተቀባይነት ቀውስ ውስጥ በወደቀበት በመጋቢት 1998 ***«አዲስ ራዕይ»*** የሚል የትንታኔ መፅሔት ጀመረ፤ በዚህ በባለ 44 ገፅ መፅሔት በቀጣይነት ሐገሪቱን እንዴት ለመምራት እንደታቀደ የዘረዘረ ሲሆን፣ የውጭ ሃይሎች አሰላለፍ ምን ሊሆን እንደሚችልም አመላከተ፤ዘላቂ ወደጆች አፍሪካዊያን፣ አረቦችና የሩቅ ምስራቅ ሐገሮች ናቸው በማለት ምዕራባዊያን ላይ ያለውን ጥርጣሬና ጥላቻ አንፀባረቀ፤ይህ ፅሑፍ ትኩረት የሚሰጠው ኢሕአዴግ ዲሞክራሲን ባድፋፋበት ወቅት ስለቀረበ ብቻ ሳይሆን፣ በፓርቲው ውስጥ የሚገኝ ወሳኝ ሠው እንደፃፈው ለመረዳት የማያስቸግር ጭምር በመሆኑ ነው፤ *ታደሰ ገብረ ወልድ* በሚል ስም «**ምርጫ እና የውጭ ግንኙነታችን**» በሚል ርዕስ የቀረበው ፅሑፍ ከመነሻው በፓርቲው ውስጥ ባለ ወሳኝ ሠው እንደተፃፈ መጠራጠር የሚቻል ሲሆን፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገብረአብ «የጋዜጠኛው ማስታወሻ» በተባለው መፅሐፉ ላይ *«ታደሰ ገ/ወልድ»* የጠ/ሚ/ር መለስ የብዕር ስም እንደሆነም ነግሮናል፤ከዚህም በመነሳት የፓርቲውና የሀገሪቱ ሁሉም ነገር በሆኑ ሰው የተፃፈ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለይ ልማትን እንዴት ለመተግበር እንደተነሱ የዘረዘሩትን እዚህጋ መመልከቱ ወይንም ማስታወሱ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ፅሁፉ ምዕራባውያን ኢህአዴግን እንደሚጠሉና በቅንጅት ፓርቲ ለመተካት ሲንቀሳቀሱ ስለመቆየታቸው ይዘረዝራል፣የአንዳንዶች ምዕራባውያን ጠላትነትም ለዘለቄታው የሚቀጥል መሆኑን በማብራራት አቅማችንን ማጠናከር አለብን ይላል፤ለዚህም በባንኮች የተከማቸ በርካታ ገንዘብ ለልማት ተግባር መዋል እንዳለበት እንደሚከተለው ይዘረዝራል

***«... ከምዕራቡ ዓለም ጋር የሚኖረን ግንኙነት ተገለባባጭ ከሆነው የእርዳታ ግንኙነት ተላቆ በቀላሉ ወደ ማይገለባበጠው የሁሉም፣ የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት እንዲሸጋገር ማድረግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ከሂደቱ የተ ማርነው ሁለተኛ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ማለት ነው... የራሳችንን አቅም ከመገንባት አኳያ ዋናው ጉዳይ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችንን ማዳበር ነው፤ <u>እንደሚታወቀው ሁሉ በባንኮች ውስጥ ለልማት ስራ ያልዋለ በቢሊዮች የሚቆጠር ብር አለ፤</u> ይኸው ገንዘብ በግል ኢንቨስትመንት መልኩም ሆነ በመንግስት የልማት ኢንቨስትመንት መልኩ ጥቅም ላይ ቢውል የአገራችንን ልማት በማፋጠን ረገድ እጅግ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል መገመት ይቻላል...»*** *(ሰረዝ የተጨመረ)*

ፅሁፍ እንዳለውም ከባንክ ለ «ግል ባለሐብቶች» ገንዘብ በመለቀቁ ከምርጫ 97 በኋላ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚታየው የሕንፃ ግንባታ ለከተማዋ እድገትና ውበት እየሰጠ መሆኑ ግልፅ ነው፤ግልፅ ያልሆነው ነገር በባንኮች የተቀመጠው ገንዘብ ቀደም ሲል ያለ ሥራ ሲከማች መኖሩ ነው፤ በዚህ በሕንፃ ግንባታ በኩል ከመንግስት ባንኮች በብድር አሰጣጥ ላይ የሚነሱና ከመመዘኛ ውጭ አድሎ የሚደረግላቸው ሰ ዎች ስለመኖራቸው የሚጠቀስ ሲሆን፣የመነሻ 30 በመቶ ሳይኖራቸው በመንግስት ባለስልጣናት ትዕዛዝ ብድር እያገኙ፣እና መሬት እየተሰጣቸው የሕንፃ ግንባታውን የሚቀላቀሉ መኖራቸው ብዙ የተባለበት ነው፤በሌለም

በኩል በሐገሪቱ ባለው ግሽበት (inflation) እና የብር የመግዛት አቅም መዳከም ሳቢያ ተበዳሪዎች ለባንኮቹ የሚመልሱት ገንዘብ በወለድ ሳይሆን፣ እንዲያውም ባንኩ ለነርሱ ወለድ እየከፈላቸው ነው በሚል በጠንካራ ሙያዊ ትንተና ከኢኮኖሚስቶች የሚነሳውን መከራከሪያ መንግስት ትኩረት አልሰጠበትም፤በዚህ በሕንፃው ግንባታ ከገገርው ፓርቲ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች የባንክ ብድር ለመክፈል ባለመቻላቸው ሕንፃቸው በባንክ በሐራጅ ሊሸጥ ሲል እዳውን ወደ ሌላ መንግስት ባንክ በማዛወርና በመሳሰሉት ወደጆችን የመጠበቅ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውም እዚህ ላይ ማንሳት የአዋጁን በጆሮ የማለት ያህል ነው፤በአጠቃላይ ከእዚህ ሕንፃ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከስርዓቱ ጋር ቅርበትና ቁርኝነት ያላቸው በብዛት እንደገቡበት ሲታመን፣ ነፃ የሆኑ ሰ ዎችም በአቅማቸው እንደተቀላቀሉም ይታወቃል።

የሕወሓት የንግድ ተቋም የሆነው ኤፈርት (EFFORT) በቦሌ መንገድ ከገነባውና በያንሰ 10 ዓመታት ካስቆጠረው ዘመናዊው «ሜጋ» ሕንፃ ጎን ሌላ አዲስ ሕንፃ ጀምሯል። ሌላው የኢህአዴግ የጫካ ሬዲዮ የነበረውና የአዲስ አበባ ከተማ ሲገባ «ፋና» በሚል ስያሜ በ1987 የሬዲዮ አገልግሎቱን የቀጠለው ጣቢያም በከተማዋ የራሱን ግዙፎ ሕንፃ የገነባ ሲሆን፣ሌላው ተያያዥ ክንፍ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልም ሕንፃ ገንብቷል፤መንግስታዊው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ አሁንም በከተማዋ ዳር ቪላ ቤቶች ውስጥ ሲገኝ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ደግሞ በደርግ ዘመነ መንግስት ቡና ገበያ ባሰራው ሕንፃ ውስጥ ከከተመ ዓመታት ተ ቆጥረዋል፤የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትም በተመሳሳይ በደርግ ዘመን በተሰራ መለስተኛ ሕንጻ ውሰጥ ይገኛል፤የመንግስቶቹ ሚዲያዎች ሕንፃ የመገንባት አቅም እንዴት አነሳቸው? ለእነያ የሚደረግ ድጋፍና ብድር ለነዚህስ ለምን አይሰጥም ብሎ መጠየቅ ይቻል ይሆን?... ከዚህ ስንነሳ በከተማዋ ከተገነቡት ሕንፃ ዎች በይፋ ከሚታወቁት ቢያንስ አራቱ የራሳቸው መሆናቸውን ያረጋግጣል።

እነዚህ በይፋ የሚታወቁ ሲሆኑ፣ከፓርቲው ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ወዘተ ላይ ጥናት ቢደረግ በከተማው ከተሰሩት ሕንፃዎች ምን ያህሉ ከንክኪ ነፃ ናቸው የሚለውን ይመልሳል፤ከመሬት የማግኘ ት ሂደት እስከ ብድር ስርዓቱ የሐገሪቱንና የባንኮችን ሕግ በጠበቀ መልኩ በነፃ ውድድር የተከናወነ መሆኑ ሊመረመር የሚገባው ነው።በመንግስት ደረጃ እየተሰሩ ያሉና የተሰሩ ሕንፃዎች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት የፌዴራል ፖሊስ ሜክሲኮ የገነባው ዘመናዊ ሕንፃ ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ በፅ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ፣ የድንገተኛ አደጋ መከላከያዎች በአራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ፅ/ቤቱ የጀመሩት፣ የገቢዎች ሚነስቴር ያስገነባው በመንግስት ከተሰሩት ጥቂት ሕንፃዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ሲሆን፣ አንዳንድ ቀበሌዎችም እንደ አቅም ኮንዲሚኒዬም ገንብተው ለቢሮ እየተጠቀሙበት ነው።

የኮንዶሚኒየም ቤቶች በከተማዋ የቤት እጥረት ላይ ችግርን በመቅረፍ ሚናቸው የሚታይ ቢሆንም፣ የሕንፃዎቹ አሠራር ደረጃ በጣም የወረደ ከመሆኑ ባሻገር አቀማመጣቸውና ቀለማቸው በዘላቂው የከተማዋን ውበት የሚጎዳ ስለመሆኑ የስነ ሕንፃ ባለሙያዎች በግልፅ ስጋታቸውን እየገለፁ ነው፤ በደርግ ዘመን በመንግስት ወጪ በቦሌ መስመር የተሰሩ አፓርትመንቶች ከዛሬዎቹ ኮንደምኒየም ቤቶቹ ጋር

ሲነፃፀሩ በደርግ ዘመን የተሰሩት ቤቶች ውበትና ደረጃ ላቅ ያለ ነው፤ቪላ እና ደጀፍ ቤት በሚል ደረጃ ሊቀመጡ የሚችሉ ናቸው፤የኢህአዴግ መንግስት ለቤት ግንባታ መነሳቱ ካልቀረ የሕንፃዎቹን ከፍታና ውበት በመጨመር፣የብድር ጊዜውን በማራዘም የከተማወዋን ውበት እና የመሬት ዕጥረትን በጠበቀ መልኩ የቤት ችግሩን መፍታት እንደሚቻል ባለሙያዎች የሚመክሩት ቢሆንም ሰሚ ያገኙ አይመስልም፤ምናልባት በልደታ አካባቢ እየተሰራ ያለው ለባለሙያዎቹ መልስ ይሰጥ ይሆን?

የኢሕአዴግ ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው በመቶ ዓመታት በሀገሪቱ ያልተሰሩ ግንባታዎች በኢሕአዴግ ዘመን እየተገነቡ ስለመሆናቸው እየገለጹ በመሆናቸው ይህንን በተመለከተም ጥቂት አብነቶችን እንመልከት፤በነገስታቱ ዘመን ይህ ተሰራ፣በደርግ ደግሞ ይህ ተገንብቷል የሚለውን ማነጻፀሪያ እንተወውና መንግስታቱ በዕርዳታ፣በብድርና በግብር ወዘተ የሚሰበስቡት ዓመታዊ ገቢ ምን ያህል እንደሆነ ስናነፃፅር የሚታየው ርቀት አንድን የገጠር ወፍጮ ቤት ባለቤት ከሼህ መሀመድ አላሙዲን ጋር የማወዳደር ያህል ይሆናል፤የኢህአዴግ መንግስት በእርዳታና ብድር እንዲሁም በግብር በአንድ ዓመት የሚያገኘው ገንዘብ የደርግ መንግስት በ17 ዓመት በሥልጣን ዘመኑ ካገኘው የሚበልጥ መሆኑንም እዚህ ጋር ማስታወሱ ተገቢ ነው::

ኢሕአዴግ ባለፈው 2002 ዓ.ም በእርዳታና ብድር ከ33 ቢሊዮን ብር በላይ ሲያገኝ፣ በግብር በኩል የሰበሰበው ደግሞ 35 ቢሊዮን ብር ያህል መሆኑን ራሱ መንግስት በይፋ አስታውቋል፤ይህ በአንድ አመት የተገኘው ገንዘብ ደርግ ገቢው በአንጻራዊ መልኩ እየጨመረ ከመጣበት ከመጨረሻዎቹ 10 ዓመታት ማለትም ከ1974 እስከ 1983 ካገኘው አጠቃላይ ገቢ 35 ቢሊዮን 724 ሚሊዮን ብር ጋር ሲነፃፀር በትንሹ የ29 ቢሊዮን ብር ብልጫ

**የደርግ መንግስት አጠቃላይ ገቢ እና ወጪ ከ1974 እስከ 1983**

የመንግሥት ገቢና ወጪ
GENERAL GOVERNMENT REVENUE AND EXPENDITURE

ሠንጠረዥ ተ.1 TABLE K.1 በሚሊዮን ብር IN MILLION BIRR

| በጀት ዓመት | ገቢ | | | ወጪ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | ከሀገር ውስጥ | ከውጭ ሀገር | ድምር | ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ | የካፒታል ወጪ | |
| 1974 | 2406.9 | 1859.6 | 547.3 | 2887.7 | 1838.6 | 1049.1 | 1981/82** |
| 1975 | 2777.8 | 2100.0 | 677.8 | 3325.2 | 2043.5 | 1281.7 | 1982/83** |
| 1976 | 2897.6 | 2255.3 | 642.3 | 3459.8 | 2224.8 | 1235.0 | 1983/84** |
| 1977 | 3243.0 | 2381.1 | 861.9 | 3983.1 | 2419.3 | 1563.8 | 1984/85** |
| 1978 | 3525.7 | 2479.0 | 1046.7 | 4398.4 | 2466.9 | 1931.5 | 1985/86** |
| 1979 | 3681.9 | 2697.8 | 984.1 | 4593.9 | 2638.8 | 1955.1 | 1986/87** |
| 1980 | 3995.7 | 2894.4 | 1101.3 | 5133.1 | 3097.1 | 2036.0 | 1987/88** |
| 1981 | 4328.2 | 3047.9 | 1280.3 | 6042.2 | 3758.5 | 2283.7 | 1988/89** |
| 1982 | 4417.6 | 2985.4 | 1432.2 | 6539.1 | 4153.5 | 2385.6 | 1989/90** |
| 1983 | 4449.6 | 3280.0 | 1169.6 | 4913.2 | 3699.2 | 1214.0 | 1990/91 |

**ጠቅላላ የ10 ዓመት የገቢ ድምር 35 ቢሊዮን 724 ሚሊዮን ብር ብር**

ምንጭ፡-የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

አለው፤በፈረንጆች 2008 ብቻ የኢህአዴግ መንግስት ከለጋሾች ያገኘው ድጋፍ 3ቢሊዮን 327 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፣ ይህን በአዲሱ ምንዛሪ ትተን በወቅቱ ምንዛሪ ወደ ብር ብንለውጠው 45 ቢሊዮን ብር ይመጣል፤በአጭሩ ደርግ 17 ዓመታት ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በአጠቃላይ በእርዳታም፣በብድርም ፣በግብርም በሁሉም ከሰበሰበው ገቢ የሚበልጠውን ኢሕአዴግ በአንድ ዓመት እያገኘ ነው፡፡

| ኢሕአዴግ በ5 ዓመት ከለጋሾች ብቻ ያገኘው የገንዘብ መጠን (ዓመቱ እ.ኤ.አ) | | |
|---|---|---|
| ዓመት (እ..ኤ.አ) | የ ገንዘብ መጠን በዶላር | የ ገንዘብ መጠን በብር ( በቀድሞው የብር ምንዛሪ 13.50 ) |
| **2004** | **1 ቢሊዮን 809 ሚሊዮን** | **24 ቢሊዮን 421 ሚሊዮን 500 ሺ** |
| **2005** | **1 ቢሊዮን 910 ሚሊዮን** | **25 ቢሊዮን 785 ሚሊዮን** |
| **2006** | **1 ቢሊዮን 941 ሚሊዮን** | **26 ቢሊዮን 203 ሚሊዮን 500 ሺ** |
| **2007** | **2 ቢሊዮን 563 ሚሊዮን** | **34 ቢሊዮን 600 ሚሊዮን 500 ሺ** |
| **2008** | **3 ቢሊዮን 327 ሚሊዮን** | **44 ቢሊዮን 914 ሚሊዮን 500 ሺ** |
| **ድምር** | **11 ቢሊዮን 550 ሚሊዮን** | **155 ቢሊዮን 925 ሚሊዮን** |

ምንጭ፡-OECD (የለጋሾቹ ማህበር) - 2010 (እ.ኤ.አ)

ዕውነቱን እንነጋገር ካልን ይህም የኢሕአዴግ ፖሊሲ ውጤት ሣይሆን በዓለም ላይ የሶሻሊዝም ስርዓት መንኮታኮትን ተከትሎ ዓለም ወደ ነፃ ገበያ መስመር የመግባቱ ግፊት ነው፤የግል ባለሀብት ተሳትፎ በደርግ ጊዜ ከነበረበት የግማሽ ሚሊዮን ብር ገደብ ዛሬ ያለገደብ እስከ ቢሊዮን ብሮች እንዲንቀሳቀስ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አግዘዋል፤ያም ሆኖ በፓርቲ ኩባንያዎች ተፅዕና እና ገዢው ፓርቲ ከዕዝ ኢኮኖሚ አስተሳሰቡ ጠቅልሎ ባለመውጣቱ ወዘተ የግል ባለሐብቱ ተሳትፎ መሄድ በሚገባው ርቀት አልሄደም፤የግል ባለሐብቱ ተሳትፎ እንዲጎለብት የሶሻሊዝም ካምፕ መፈራረስ አስተዋፅኦ እንዳደረገው ሁሉ፣ለውጭ ዕርዳታ መጨመርም ሀገሪቱ የምዕራባውያኑን የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መከተሏ ጠቅሟል፡፡


የቀደመው ወታደራዊ መንግስትም ሞት ቀደመው እንጂ ሽርተት ማለት ጀምሮ ነበር፤የደርጉ ም/ሊቀመንበር የነበሩት ሻለቃ አጥናፉ አባተ ከመነሻው ያቀነቀኑትንና እንደወንጀል ተቆጥሮ ለሞት ያበቃቸውን የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ወደ ሞት ጉዞ በጀመረበት በየካቲት 1982 ተቀብሎ ከሶሻሊዝም የዕዝ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መላቀቅ ጀምሮ እንደነበር በአዋጅ የተነገረ ነውና አይዘነጋም፤የሶሻሊዝም ርዕዮት በዓለም ላይ የተቀናቃኝነት ሚናውን ካጣ በኋላ ደርግ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ሙሉ በሙሉ የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ መግባቱ ከግዜው አስገዳጅነትና ከጅምር እንቅስቃሴው አንፃር የሚጠበቅ ነበር፤በተመሳሳይ የሶሻሊዝም ካምፕ ፈርሶ ካፒታሊዝም የበላይነት እስከያዘበት ግዜ ድረስ የሶሻሊዝም

ያውም አጥባቂ ፍልስፍናቸውን የአልባንያ መሪ ከነበሩት ኤንቨር ሆጃ ሲቀዱ የነበሩት ኢሕአዴጎችም ወደ ገበያ ኢኮኖሚ የተሸጋገሩት በአለም ዓቀፋዊው ሁኔታ አስገዳጅነት መሆኑን መገመት አያስቸግርም፡፡

ዛሬም ይህንኑ በሙሉ ልብ መያዝ አቅቷቸዋል፤ካልጠፋ ሐገር ሩቅ ምስራቅ ካለችው ትንሽ ሀገር ላኦስ በቀር በአለም ላይ የሌለ አብዮታዊ ዲሞክራሲን የሙጥኝ ማለታቸው ከሶሻሊዝም ፍልስፍና ጋር ወደቁት ፍቅር ጥልቅ ለመሆኑም አመላካች ነው፤በአጭሩ ለማለት የፈለኩት የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲን መከተል የጀመሩት በህይወት ለመኖር የነበራቸው ምርጫ እሱ ብቻ ስለነበረ እንጂ የብልፅግና ጎዳናው ይህ ነው ብለው ስለተነሱ አልነበረም፡፡

የገቢ መጨመር እና የእርዳታውም መጉረፍ መነሻው ይህ ነው፤በተለይ ከፈረንጆች 2001 በኋላ ዕርዳታ በዓለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል (7.2 ％)፤ለዚህም መነሻ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፤ መስከረም 1ቀን 1994 (9/11) በአሜሪካ ላይ የተሰነዘረውና ከ3000 የሚልቁ ንጹሀንን የቀጠፈው የሽብር ድርጊት አሜሪካ ዓላማዎቿንና ፖሊሲዎቿን በማደግ ላይ ወደሚገኙ ሐገራት ለማስረፅ የእርዳታ ልገሳዋን ከፍ በማድረግ የፀጥታ፣ የልማትና የዲፕሎማሲ ትብብርን ወደ ማጠናከር ተሸጋጋረች፤በፈረንጆች 2001 ዓ.ም 11 ቢሊዮን 429 ሚሊዮን ዶላር የነበረውን ዕርዳታ በ2002 ወደ 13 ቢሊዮን 290 ሚሊዮን ዶላር ከፍ አደረገች፤ይህም ማለት ከአጠቃላይ ብሄራዊ ገቢዋ በ2001 ዓ.ም 0.11％ ለርዳታ ስታውል፤በ2002 ወደ 0.13％ አሳደገችው፤አሁንም ይበልጥ እየጨመረ ይገኛል፤በ2007 ዓ.ም. 21 ቢሊዮን 787 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ሲል በ2008 ደግሞ ወደ 26 ቢሊዮን 842 ሚሊዮን አሳድጋዋለች፤ይህም ከአሜሪካ ብሄራዊ ገቢ (GNI) 0.19 ％ ማለት ነው፡፡ከአሜሪካ ብሄራዊ ገቢ 0.2％ እንኳን የማይሞላው ለኢትዮጵያ የ6 ዓመት በጀት የሚበቃ መሆኑን ሳሰላ የአሜሪካ ድምፅ የአማርኛውን አገልግሎት ለማፈን ስለመወሰናቸው የኢሕአዴግ መሪዎች የሰጡት

**በ 2008 ( እ.ኤ.አ) ዋናዎቹ ተለጋሾች እና ለጋሾች**




**1.1.1. Top 10 ODA receipts by recipient**
*USD million, net disbursements in 2008*

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | Iraq | 9 870 | 8% |
| 2 | Afghanistan | 4 865 | 4% |
| 3 | Ethiopia | 3 327 | 3% |
| 4 | Palestinian Adm. Areas | 2 593 | 2% |
| 5 | Viet Nam | 2 552 | 2% |
| 6 | Sudan | 2 384 | 2% |
| 7 | Tanzania | 2 331 | 2% |
| 8 | India | 2 108 | 2% |
| 9 | Bangladesh | 2 061 | 2% |
| 10 | Turkey | 2 024 | 2% |
| | Other recipients | 94 494 | 73% |
| | **Total** | **128 608** | **100%** |

**1.1.2. Top 10 ODA donors**
*USD million, net disbursements in 2008*

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | United States | 23 860 | 19% |
| 2 | EU institutions | 14 428 | 11% |
| 3 | Germany | 9 063 | 7% |
| 4 | United Kingdom | 7 367 | 6% |
| 5 | Japan | 6 823 | 5% |
| 6 | IDA | 6 689 | 5% |
| 7 | France | 6 461 | 5% |
| 8 | Saudi Arabia | 5 544 | 4% |
| 9 | Netherlands | 5 200 | 4% |
| 10 | Spain | 4 802 | 4% |
| | Other donors | 38 373 | 30% |
| | **Total** | **128 608** | **100%** |

**1.1.3. Trends in ODA**

| | 2007 | 2008* | % change |
|---|---|---|---|
| ODA net disbursements (2007 USD million) | 107 102 | 122 253 | 14.1% |
| ODA commitments (2007 USD million) | 126 266 | 149 162 | 18.1% |
| Population (thousands) | 5368 331 | 5416 970 | — |
| Net ODA per capita (USD) | 20.0 | 23.7 | — |

* Saudi Arabia and Turks and Caicos Islands left the DAC list of ODA Recipients in 2008

*ይህ ቻርት የተወሰደው ከለጋሾቹ ማህበር OECD የ 2010 ሪፖርት ሲሆን፤በ2008 በዓለም ላይ ከፍተኛ ልገሳ ያገኙ 10 ሀገራትን (ከላይ) እና ዋናዎቹን ለጋሽ 10 ሀገራት ያሳያል፤በቻርቱ ላይ እንደሚታየው በአመቱ ኢትዮጵያ ከኢራቅና አፍጋኒስታን ቀጥሎ በዓለም ላይ ሶስተኛዋ ተለጋሽ ሀገር ሆናለች፤ኢራቅና አፍጋኒስታን ከ1994 እና ከ1996 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ወዲህ በቀውስ ውስጥ የሚገኙ ሀገር መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በቻርቱ ላይ ODA በሚል ምህፃረ ቃል የተቀመጠው አጠቃላይ የልማት ድጋፍ ( all development*

*መግለጫም ታወሰኝ፤የጎረቤታችን የጋሽ ኑሪ ተረትም ኮረኮረኝ «የዋቤ ጅረት ከጊቤ ወንዝ ጋር እፎካከራለሁ ብሎ ተፈናጥቆ አለቀ» ...*

*ሥለ ዓለም ዓቀፍ ዕርዳታ የጀመርነውን እናጠቃለው፤ለዕርዳታ መጨመር ምክንያት የሆነው* ሌላው ነጥብ የሚሊዬኔሙን የልማት ግቦች (MDGs) ለማሳካት ባለፀጎቹ ከአመታዊ ብሄራዊ ገቢያቸው (GNI) 0.7 % ለታዳጊ ሀገራት እንዲሰጡ የተባበሩት መንግስታ በፈረንጆች 2000 ያሳለፈው ውሳኔ ተከትሎ በ*OECD (organization for economic co-operation & development*) የታቀፉ ለጋሽ ሀገራት እ.ኤ.አ በመጋቢት 2002 በሜክስኮ ባካሄዱት ስብሰባ እርዳታን ለመጨመር መስማማታቸው ታዳጊ ሀገራት ይበልጥ የእርዳታ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እድል ፈጥሯል፤ያም ሆኖ እስካሁን የተባበሩት መንግስታት በወሰነው መሰረት ከብሄራዊ ገቢያቸው እርዳታን ወደ 0.7 ያደረሱና ከፍ ያደረጉ ሀገራት ስዊድንና ኖርዌይን ጨምሮ አምስት ሀገራት ብቻ ናቸው፤በቀሪዎቹ አምስት ዓመታት የሚሊኒየሙን ግብ ለማሳካት ይረዳ ዘንድ ለጋሾች እርዳታቸውን ለመጨመር በኒውዮርክ ሰሞኑን በተካሄደው የመሪዎች ጉባኤ ላይ ቃል እየገቡ በመሆናቸው በቀጣይም እርዳታ እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡

ስለዕርዳታ አሰጣጡ ሂደት መዘርዘር ያስፈለገው የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ለዕርዳታው መጨመር የኢሕአዴግ አስተዋፅኦ አለ የሚል አላስፈላጊ ሙግት ውስጥ እንዳይገቡና ይልቁንም በእርዳታና በብድር የተገኘው ከአራት መቶ ቢሊዮን ብር በላይ የት ገባ የሚለውን አብረን እንድንጠይቅ ነው፡፡ ዕርግጥ ነው ኢሕአዴጎች መድብለ ፓርቲ ሥርዓት፣የፕሬሥ ነጻነት ወዘተ ለሚሉት ቅድመ ሁኔታዎች እምቢኝ ብለው እርዳታ እንዳያጡ ወይንም እንዳይቀንስባቸው ጥያቄዎቹን «*ሥጋ ሰጥቶ* **ቢላዋ በመከልከል** » እየመለሱ መሆኑ እርግጥ ነው፤(***መደራጀት ይቻላል መንግስት መሆን ግን አይፈቀድም፤መጻፍ ይቻላል፤ግን ስለ ልማት እንጂ ስለሚታየው ግፍና በደል፣ስለስርዓቱ ጉድለት ማንሳት አይቻልም***) ...ሰለ እርዳታው ሂደትና ስለተገኘው ገንዘብ በመጠኑ ይህን ያህል ካየን በኢትዮጵያ ብዙ ስለሚነገርላቸው ግንባታዎች እንመልከት፡፡

ወደ መንገድ ግንባታው ስናመራ ይህ ዘርፍ በዋናነት የውጭ እርዳታን መሠረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን በአዲስ አበባ ለመንገድ ግንባታ የዋለው ወጪ አንዳንድ የከተማዋ ባለስልጣናት እንደሚናገሩት 9 ቢሊዮን ብር ሲሆን፤መረጃዎች እንደሚያሳዩት ግን ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በአዲስ አበባ ለመንገድ ግንባታ የዋለው ብር 6.3 (ስድስት ነጥብ ሶስት) ቢሊዮን ብር ነው፤ብዙውን ግዜ የቁጥር ልዩነት የሚመዘገበው በግንባታው ወቅት የነበረውን የብር ምንዛሪ መጠን ከመጠቀም ይልቅ ብዙ ገንዘብ አውጥተናል ለማለት በወቅታዊው የብር ምንዛሪ መጠን እያሰሉ የመንግስት ባለስልጣናት ስለሚጠቀሙ ነው የሚል ግምት አለ፤ለምሳሌ የአዲስ አበባው የቀለበት መንገድ የወጣበት ወጪ 520 ሚሊዮን ብር ያህል ሲሆን፣ይህንን አሁን ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት እንደሆነ እየተነገረ ነው፤ በፌዴራል ደረጃ የተዘመገበውና ለመንገድ ግንባታ የወጣው (የአዲስ

አበባውን ይጨምር አይጨምር የተሟላ ሪፖርት የለም) 45.3 ቢሊዮን ብር ነው።

ሥለ መንገድ ሲነሳ የኢህአዴግ መንግስት ብዙ የሚያወራለት የጎተራው መተላለፊያ (inter-change) መንገድን ነው፤ (መጀመሪያ አካባቢ መንገዱ ስለሚያደናግር Confusion road ሲባል ነበር) ኢህአዴግ እንደ ትልቅ ስኬት የሚያነሳወና በምርጫ ቅስቀሳ ፖስተሩ ላይ ጭምር የለጠፈው ይህ መንገድ ርዝመቱ 8.1 ኪሎ ሜትር ነው፤በታህሳስ 1999 ተጀምሮ በግንቦት 2001 ነው የተጠናቀቀው፡፡መጀመሪያ ላይ 96.1 ሚሊዮን ብር ከተ ገመተ በኋላ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የሆነበት ይህ ውብ መንገድ ወጪው መቶ በመቶ በቻይና መንግስት የተሸፈነ መሆኑ ለሕዝብ በሚገባ አልተገለፀለትም።በተመሳሳይ የኢሕአዴግ ሌላው ስኬት ተደርጎ የሚወሰደው በአባይ ወንዝ ላይ የተሰራው እና ዘመናዊው 303 ሜትር የሚረዝመው የአባይ ድልድልይ (ሕዳሴ ድልድይ ተብሏል-) ወጪው መቶ በመቶ በጃፓን መንግስት የተሸፈነ ነው፤በኢትዮጵያ በርዝመቱ 3ኛ ድልድይ ነው፤የተመረቀው በ2000 መግቢያ ላይ ነው፤እነዚህ መንግስታት በተዘዋዋሪ ለሚያገኙት ጥቅምም ይሁን ለቸርነት ላደረጉት ተግባር በቂ ምስጋና ማቅረብና ሕዝብም ይህንኑ እንዲገነዘብ ማድረግ ሲገባ የተያዘው መንገድ መሸፋፈን እና የኢሕአዴግ መንግስት በፈጠረው አቅም የተገነባ እንዲመስል ማድረግ ነው፡፡

በእነ ቻይና ዕርዳታ መሠራቱ ቢነገርም እኮ በኢሕአዴግ የስልጣን ዘመን በመሰራቱ አብረው መነሳታቸው የግድ ነው፤የጎተራው ዘመናዊ መተላለፊያ መንገድ ከውበቱ ባሻገር ለትራፊክ ፍሰቱ የሰጠው ጠቀሜታ ሲታይ በቦሌ፣በሚክስኮ አደባባይ፣በመገናኛ ወዘተ የሚታዩ መጨናነቆችን በተመሳሳይ ማስወገድ የሚያስችል የውጭ እርዳታ እየጎረፈ ከነችግራችን መቀጠላችን ያሳዝናል፤የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በቦሌ መስመር መንገዱን ለማስፋት እና በሶስት ቦታዎች ላይ ማለትም በኦሎምፒያ፣በወሎ ሰፈር እና በርዋንዳ መገንጠያ ላይ የላይ መተላለፊያ (by-pass) መንገድ ለመስራት ጨረታ ከወጣ በኋላ በተደጋጋሚ የተሰረዘው በገንዘብ እጦት ነው፤በዓመት ከ40 ቢሊዮን በላይ እርዳታና ብድር እየታፈሰ መቶ ሚሊዮን ብሮች በመጥፋቱ ደሴቱ ላይ ሰንሰለት በማሰር ማስዋብ እንደአማራጭ ተወስዷል፤

ከመንገድ ቀጥሎ በስፋት የሚነሳው በኢሕአዴግ ዘመን የተሠሩት ኢሕአዴጋውያን የሚመኩባቸው የኃይል ማመንጫዎች ናቸው፤ ጥር 5/2002 ተመርቆ ወር እንኳን ሣይሠራ የዋሻ መደርመስ የገጠመው ግለገል ጊቤ -፪ 420 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው ሲሆን፣ የፈጀው ገንዘብ 373 ሚሊዮን ዩሮ ወይንም በወቅቱ ምንዛሪ 5 ቢሊዮን ብር ያህል ነው። ከዚህ ውስጥ 220 ሚሊዮን ዩሮ በጣሊያን መንግስት 50 ሚሊዮን ዩሮ በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ነው የተሸፈነው፤ተከዜም 3.9 ቢሊዮን ብር ያህል የወጣበት ሲሆን፣ ትልቁ የሃይል ማመንጫ ጣና በለስ ደግሞ በአጠቃላይ ወደ 7 ቢሊዮን ብር ፈጅቷ ል፤እዚህ ላይ እንደሚታየው ለሃይል ማመንጫዎች የወጣው ወጪ ወደ 16 ቢሊዮን ብር ያህል ነው፤ለመንገድ ዘርፍ የወጣው 45.3 ቢሊዮን ብር ሲታከል ወደ 61.2 ቢሊዮን ብር ይደርሳል፤ለአዲስ አበባ

መንገድም የወጣውን ወጪ ከፌደራል ውጪ ነው ብለን በመውሰድ፣ትክክለኛውን ወጪ 6.3 ቢሊዮን ብር ትተን እነሱ የሚሉትን 9 ቢሊዮን ብር ስንጨምርበት 70.2 ቢሊዮን ብር ይሆናል፤ኢሕአዴጎች መብትና ነጻነታችንን ለመግፈፋቸው እንደ ማካካሻ የሚያወሩልን ይህ ነው፤የሚወራለት መንገድን የሚወራለት ኃይል ማመንጫ በጠቅላላ በ19 ዓመት 70.2 ቢሊዮን ብር የወጣበት ነው፤ እርግጥ ነው 70.2 ቢሊዮን ብር ትንሽ አይደለም፤ በጣም ከፍተኛ ገንዘብ ነው፤የቦሌው አዲሱ የመንገደኞች ማረፊያ እና የአየር መቆጣጠሪያ ማማ ወጪ 1.5 ቢሊዮን ብርንም ጨምሩበት፡፡

1.2.9. ODA by recipient country

USD million, 2007 prices and exchange rates, top 50 recipient countries since 1970, net ODA receipts

| | 2000-08 | 1970-79 | 1980-89 | 1990-99 | 2000-08 |
|---|---|---|---|---|---|
| | Share(%) | Annual averages | | | |
| Afghanistan | 2.5 | 231 | 70 | 309 | 2 442 |
| Algeria | 0.4 | 555 | 366 | 367 | 356 |
| Bangladesh | 1.6 | 1 876 | 2 801 | 2 005 | 1 571 |
| Bolivia | 0.9 | 241 | 499 | 835 | 834 |
| Burkina Faso | 0.8 | 316 | 496 | 577 | 768 |
| Cameroon | 1.0 | 431 | 505 | 737 | 1 016 |
| China | 1.7 | 4 | 1 810 | 3 100 | 1 693 |
| Colombia | 0.7 | 401 | 187 | 217 | 693 |
| Congo, Dem. Rep. | 2.1 | 747 | 964 | 400 | 2 020 |
| Cote d'Ivoire | 0.5 | 351 | 458 | 1 160 | 464 |
| Egypt | 1.4 | 4 306 | 2 982 | 3 904 | 1 388 |
| Ethiopia | 2.1 | 373 | 1 076 | 1 249 | 2 053 |

*የተገኘው የእርዳታ መጠን በዚህ የOECD-2010 ሪፖርት ቻርት ላይ የተመለከተው ነው፣በፈረንጆች 1991 የኋለኞቹን 8 ወራት ስልጣን ላይ የነበረው ኢሕአዴግ ቢሆንም፣ከላይ የተቀመጠው የዕርዳታ ድምር ከ1992 ወዲህ ያለውንና ሙሉ*

ይህ ከሆነ ታዲያ የኢህአዴግ መንግሥት የማይወደስበትና የማይዘፈንለት የሚሰራው መንግስታዊ ግዴታው ስለሆነ ወይንም በማካካሻነት መብትና ነፃነታችንን ስለገፈፈ ብቻ አይደለም፤በስልጣን ዘመኑ እ.ኤ.አ እስከ 2008 ከዋናዎቹ ለጋሾች (እነ ቻይናን ሳይጨምር ) በእርዳታ እና በብድር ከሰበሰበው 28 ቢሊዮን 469 ሚሊዮን ዶላር (በቀድሞው ምንዛሪ በ13.5 ስንመታው 384 ቢሊዮን 331 ሚሊዮን 500 ሺ ብር) ውስጥ የወጣው 70.2 ቢሊዮን ብር ብቻ በመሆኑ፣ከ314 ቢሊዮኑ ብር በላይ የት ደረሰ ? ለምን ለምን አገልግሎት ዋለ? የተጣራ እና ይፋ ባይሆንም የ2009 እና የ2010 ልገሳ ድምር በትንሹ ከ70 ቢሊዮን ብር በላይ በመሆኑ በአጠቃላይ ወደ 400 ቢሊዮን ብር የት ገባ ? ስንት ሆስፒታል፣ስንት ጤና ኬላ ተገነባ ? ለሀገሪቱ በብድር የተገኘው ገንዘብ እስከ ልጅ ልጆቻችን የሚወርድ ዕድ በመሆኑ ገና በሚመጡት ልጆቻችን ስም ጭምር ሙግት የምንቆምበት ጉዳይ ነው፤ የተሰጠው ዕርዳታ ሁሉ የኢኮኖሚ ዕርዳታ እንዳልሆነና የማህበራዊም ጭምር ቢሆንም፣ይህን ያህል ከፍተኛ ዕርዳታ እና ብድር እየፈሰሰ ምንም አልተሰራም ማለት ግነት ይሆናልን?

በማሕበራዊ መስክስ የሚባለውን ያህል ውጤት ተመዝግቧል? ውጤታማ የተባለው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብዙ በሚያወራለት በእናቶች እና ሕፃናት ሞት የሚሊኒዬሙን ግብ ለማሳካት ምን ያህል ተጉዟል? የዓለም ባንክ በቅርቡ ይፋ ባደረገው ጥናት ከሰሀራ በታች ከፍተኛ መሻሻል ያሳዩ በማለት ከፊት ያስቀደመው ማላዊንና ኤርትራን ነው፣ኢትዮጵያ ግን ከናይጄሪያና ከኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ኪንሻሳ) ጋር በመሆን በዓለም ላይ የሚመዘገበውን የእናቶችና የሕጻናት ሞት ግማሽ ያህሉን ብቻቸውን

መያዛቸውም በሪፖርቱ ተመልክቷል፤ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ግን የሚሊኒዬሙን ግብ በቀሪዎቹ 5 ዓመታት ኢትዮጵያ እንደምታሳካ በኒውዮርክ በተካሄደው 65ኛ የመሪዎች ጉባኤ ላይ መስከረም 11/2003 ቃል ገብተዋል፤የሚሊኒዬሙ የልማት ግብ በሚል ተዘርዝረው እ.ኤ.አ እስከ 2015 ተግባራዊ እንዲሆኑ ከታቀዱት ውስጥ አንዱ የሕጻናትን ሞት በ2/3ኛ መቀነስ፣የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ እና እንዲያጠናቅቁ ማድረግ፣በርሀብ የሚሰቃዩትን በግማሽ ማውረድ፣የዕለት ገቢያቸው 1 ዶላር (16 ብር) በታች (480 ብር በወር) የሆኑ ዜጎችን በግማሽ መቀነስ ወዘተ የሚሊኒዬሙ ግቦች በሚል የተቀመጡ ናቸው፤እነ ቻይና ፣ህንድ ፣ቬትናም የሚሊኒየሙን ግብ እያሳኩ ስለመሆናቸው ዓለም እየመሰከረላቸው ሲሆን፤የእኛ ምስክር ዛሬም ያው የእኛዎቹ ናቸው፡

ወደ ተናሰንበት ጉዳይ እንመለስ፤ኢትዮጵያ የውጭ የልማት እርዳታ ማግኘት የጀመረችው ሁለተኛው የአለም ጦርነት ካበቃበት እ.ኤ.አ ከ1945 በኋላ ሲሆን፣ይህ እርዳታ እስከ 1970 ከ20 በሚበልጡ ዓመታት 600 ሚሊዮን ዶላር ነበር፤ደርግ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ ይህም ዕርዳታ የነጠፈ ሲሆን ፣የምእራባውያኑ እርዳታ እንደገና የታየው በ1977 ድርቅ ወቅት ነበር፤በዋናነት ከቀድሞዋ ሶቬዬት ሕብረት እንዲሁም ከዓለማቀፉ የነዳጅ ማህበር OPEC ወዘተ ይለገስ የነበረው እርዳታ በአጠቃላይ ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር የተመዘገበ ቢሆንም፣በአብዛኛው ከጦር መሳሪያ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ጥናቶች ያስረዳሉ፤ደርግ ወደ መጨረሻ እርዳታውን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ጨምሮ ከሐገሪቱ በጀት 60 በመቶ ጦርነት ላይ ያውል እንደነበርም በተደጋጋሚ የተገለፀ ነው፡፡ኢሕአዴግን ከነዚህ በአብዛኛው በራሳቸው አቅም ሲፍጨረጨሩ ከኖሩና በጦርነት ውስጥ ካለፉ መንግስታት ጋር ማወዳደር ይህንን ነባራዊ ሁኔታ ካለመገንዘብ በሚመነጭ ቅንንት ፣በሌላም በኩል አታላይነት ነው፤

እናጠቃለው፤የዲሞክራሲ ጥያቄ ጨርሶ እንዳይነሳ የሚቀሰቅሱትና ሥለ ተዓምራዊው ዕድገት የሚያወሩት ኢሕአዴጎች እንደሚሉት በርግጥ መንገድ እየተሠራ መሆኑን አይተናል፤ የኃይል ማመንጫ እየተገነባ መሆኑን አስተውለናል፤ኢሕአዴግ ቀደም ባሉት ማለትም ከምርጫ 97 በፊት ከነበሩት አመታት ከነበረው የልማት ድንዛዜ ውስጥ መውጣቱ፣ ጅምር ልማት ማሣየቱ የሚዳሰስ ቢሆንም በሠበሠበው ዕ ርዳታና ብድር መሥራት ከሚገባው በጣም እጅግ ትንሹን ብቻ እየሠራ መሆኑም በመረጃ ተገላልጧል፣ የልማት እንቅስቃሴ ማሣየት ደግሞ ነፃነትና መብታችንን ለመግፈፊያ ዋስትና አለመሆኑንም እነሱም ሊረዱልን ይገባል፡፡

ይህ መንግስት ከግብር ከሚሠበሠበው ገንዘብ እንዴት የውሃ መውረጃ ቦይ ሣይሠራበት፣ከውጭ በእርዳታና በብድር ባካገኘው ገንዘብ ብቻ ተዓምር ማሳየት ቢገባውም ከላይ እንደተመለከትነው በመቶ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ለምን እንደዋለ አልታወቀም፤ለውጭ ባለሃብቶች ከሚሰጡ ሰፋፊ መሬቶች ምን ያህል አሜሪካን ዶላር ተሰበሰበ ? ከዚህ ሁሉ ስንነሳ በተሰራው መንገድ እና በተተከለው የሃይል ማመንጫ መደነቅ ሳይሆን ቀሪው ገንዘብ የት ደረሰ ብለን መቆጨት ነው የሚገባን፡፡ባለፉት ዓመታት፣ዛሬም አልፎ አልፎ ዋና ከተማችን ጭምር በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ስታልፍ፣ድፍን ኢትዮጵያችን ስትጠቁር ይህ ሁሉ የውጭ ብድርና ድጋፍ እያለ መሆኑን ለሚያገናዝብ የሚያሳምም እንጂ

የሚያኩራራ ባልሆነ ነበር፤ሕሊናቸውን በሆዳቸው ለከለሉ እና እውነት ለማይታያቸው አዲሱን የቴዲ አፍሮ ነጠላ ዜማ «ባዶ ይሁን ኪስን» በመገበዝ ልሰናበት፤ውሸት ተናግሮ ፤አንገትን ሠብሮ ጥቅም ከማግደድ አዎን በባዶ ኪስ ሠላም ይበልጣል። ...ግሩም ዜማ ነው ፈልጋችሁ ስሙት፡፡

**ለአስተያየትዎ እነሆ ኢሜል**

lualawi2000@yahoo.com

## *ለጋሾቹ እነማን ናቸው ? OECD ማነው?* organization for economic co-operation & development

ይህ የዓለማችን ለጋሽ ሀገራት ተቋም እ.ኤ.አ በ1960 በፈረንሳይ ፓሪስ በ20 ለጋሽ ሀገራት የተመሰረተ ነው፤እነሱም 1/ ኦስትርያ 2/ ቤልጂየም 3/ ካናዳ 4/ዴንማርክ 5/ፈረንሳይ 6/ጀርመን 7 /ግሪክ 8 /አይስላንድ 9/ አየርላንድ 10/ ጣሊያን 11/ ሉግዘምበርግ 12/ ኔዘርላንድ 13/ ኖርዌይ
14/ ፖርቹጓል 15/ ስፔን 16/ስውዲን 17/ ስዊትዘርላንድ 18 /ቱርክ 19/ዩናይትድ ኪንግደም20/ዩ.ኤስ.አሜሪካ ናቸው፡፡በሂደት ሌሎች10 ሀገራት ታክለውበት ዛሬ ቁጥራቸው ወደ 30 ከፍ ብሏል፤የኋለኞቹ ሀገራት 21/ጃፓን 22/ፊንላንድ 23/አውስትራሊያ 24/ ኒውዝላንድ 25/ሜክሲኮ 26/ቼክ ሪፐብሊክ 27/ሀንጋሪ 28/ፖላንድ 29/ኮርያ (ደቡብ) 30/ስሎቫኪያ -የእነዚህ ሐገራት አጠቃላይ ልገሳ ምን ያህል እንደሆነ የ2009ን እንመልከት፡-

NET OFFICIAL DEVELOPMENT ASSISTANCE IN 2009

**የልማት ዕርዳታ ለጋሾች በ2009 ለሀገራት የለገሱት ገንዘብ እና ከጠቅላላ ገቢያቸው(GNI) ለዕርዳታ የመደቡት በመቶኛ**

| ለጋሾቹ ሐገራት | አጠቃላይ ዕርዳታ<br>በአሜሪካ ዶላር | ከአጠቃላይ ሀገራዊ ገቢ በመቶኛ |
|---|---|---|
| አውስትራሊያ | 2ቢሊዮን 761ሚሊዮን | 0.29 |
| ኦስትርያ | 1ቢሊዮን 146 ቢሊዮን | 0.30 |
| ቤልጂየም | 2ቢሊዮን 601ሚሊዮን | 0.55 |
| ካናዳ | 4ቢሊዮን 13ሚሊዮን | 0.30 |
| ዴንማርክ | 2 ቢሊዮን 810 ሚሊዮን | 0.88 |
| ፊንላንድ | 1ቢሊዮን 286 ሚሊዮን | 0.54 |
| ፈረንሳይ | 12ቢሊዮን343 1ሚሊዮን | 0.46 |
| ጀርመን | 11ቢሊዮን 982ሚሊዮን | 0.35 |
| ግሪክ | 607ሚሊዮን | 0.19 |
| አየርላንድ | 1ቢሊዮን | 0.54 |
| ጣሊያን | 3ቢሊዮን 314ሚሊዮን | 0.16 |
| ጃፓን | 9ቢሊዮን 480ሚሊዮን | 0.18 |
| ኮርያ (ደቡብ) | 816ሚሊዮን | 0.10 |
| ሉግዘምበርግ | 403ሚሊዮን | 1.01 |
| ኔዘርላንድ | 6ቢሊዮን 425 ሚሊዮን | 0.82 |
| ኒውዝላንድ | 313 ሚሊዮን | 0.29 |
| ኖርዌይ | 4ቢሊዮን 86 ሚሊዮን | 1.06 |
| ፖርቹጓል | 507 ሚሊዮን | 0.23 |
| ስፔን | 6ቢሊዮን 571ሚሊዮን | 0.46 |
| ስውዲን | 4ቢሊዮን 546 ሚሊዮን | 1.12 |
| ስዊትዘርላንድ | 2ቢሊዮን 305ሚሊዮን | 0.47 |
| ዩናይትድ ኪንግደም | 11ቢሊዮን 505 ሚሊዮን | 0.52 |
| ዩ.ኤስ.አሜሪካ | 28ቢሊዮን 665ሚሊዮን | 0.20 |
| ጠቅላላ ድምር | 119 ቢሊዮን573 ሚሊዮን | 0.31 |
| በአማካይ የአንድ ሀገር ድርሻ | | 0.48 |

ምንጭ-OECD –14 april 2010

መስከረም14/2003